**#TibebBeAdebabay**

goethe.addisabeba
goethe_addis

ጥበብ በአደባባይ
THE ART SIDE OF ADDIS ABEBA
03-11 MAY 2018

GOETHE INSTITUT
Sprache. Kultur. Deutschland.

The project *Tibeb be Adebabay - The Art side of Addis Abeba* is a joint effort of eleven artist groups coordinated by the Goethe-Institut Addis Abeba. Supported by the Ethiopian Ministry of Culture and Tourism.

The Goethe-Institut is the German Cultural Institute. We promote knowledge of the German language abroad and foster international cultural cooperation between Ethiopia and Germany.




From left to right: Fekat Circus; Gamification (photo: Behailu Shiferaw); Henok Temesgen, Guitarist (photo: Behailu Shiferaw); The Little Creative Center (photo: Mulugeta Gebrekidan)

# ጥበብ በአደባባይ
# THE ART SIDE OF ADDIS ABEBA

## ጥበብ በአደባባይ ጨዋታዎችን፣ ጥበባት እና ባህልን ለአንድ ሳምንት ወደ አዲስ አበባ ጎዳናዎች መልሷቸዋል

አዲስ አበባ ብዙ ጎሳቦች ባሏቸው የፈጠራ ባለሙያዎች የተሞላች፣ ለፈጠራ የምታነሳሳ የደራች ከተማ ናት፡፡ ጥበብ በአደባባይ -የአዲሳባ ኪናዊ ገፅ ደግሞ፣ ጥበባትን ከባህል ማዕከላት አውጥቶ ወደ ከተማዋ የሕዝብ መገናኛ ጎዳናዎች እና ወደ ሰዎች የዕለት ተዕለት ኑሮ የሚያደርስ ፌስቲቫል ነው፡፡ ለአንድ ሳምንት ያህልም፣ ሁሉም ሰው - ሕፃን አዋቂ ሳይል - የየራሱን የፈጠራ ችሎታ ፈልጎ ማግኘት እና ከዝነኛ የአዲስ አበባ አርቲስቶች ጋር መገናኘትና መቀራረብ ይችላል፡፡ መገናኛ ላይ የጃዝ ባንድ ውስጥ ገብተው ሙዚቃ ይጫወቱ፣ ስድስት ኪሎ ላይ ግጥሞችን ይጻፉ፣ መስቀል አደባባይ ደግሞ የዕለት ተዕለት ህይወትዎን ወደ ጨዋታነት ይለውጡ፣ ወይም ስለኪነሕንፃ እና ከተማ ማቀድ ይማሩ፡፡ የእነዚህ ሁሉ ክንውኖች አካል በመሆን፣ ጥበብ በአደባባይን የራስዎ የፈጠራ አጋጣሚ ያድርጉት!


**የሰርከስ ጉዞ** (ገፅ 4)
**ሲኒማኛ ይናገራሉ?** - የራስዎን አጭር ፊልም ዳይሬክት ያድርጉ፣ ይቅረፁ፣ ይተውኑበት (ገፅ 5)
**ጓዳና ጎዳና** - ስለኪነሕንፃ መሠረታዊ መርሆች ይወቁ (ገፅ 6)
**የከተማው ሱቅ** - ቤቶች እና የከተማ ዲዛይን ከ“ተስፋ” አንፃር (ገፅ 7)
**ፎቶ ቀጭ ቀጭ** - የራስ ፎቶዎችን፣ መላዎችን እና ጥበቦችን በነፃ (ገፅ 8)
**ትንሿ ፈጠራ ማዕከል** - ፖርትሬት በመሳል ራስን መግለፅ (ገፅ 9)
**ተጫወች አዲሳባ** - በመማር፣ በማፍቀር እና በመኖር ውስጥ ጨዋታን መመለስ (ገፅ 10)
**ሙዚቃ - ግቡበት!** - በሙዚቃ ክዋኔዎች ይደሰቱ ወይም መሣሪያ ለመጫወት ይሞክሩ (ገፅ 11)
**እንቅመስ** - ጥበብን ማጣጣም (ገፅ 12)
**ፀሀይ** - አብራችሁኝ አንብቡ (ገፅ 13)
**ስነጽሑፍ** - አዳዲስ ሐሳቦች እናዋጣ (ገፅ 14)


## Tibeb be Adebabay brings back one week of fun, arts and culture to public spaces of Addis Abeba

Addis Abeba is an inspiring and energetic city, full of creative people with lots of ideas. *Tibeb be Adebabay – The Art Side of Addis Abeba* is a festival, which takes art from the cultural centers to the city's public spaces and into people's daily lives. For one week, everyone – adults and children - can explore and discover their own creativity and engage with famous artists from Addis Abeba. Play in a Jazz band in Megenagna, write short poems in Sedist Kilo, gamify your everyday life in Meskel Square or learn about architecture and urban planning. Be part of all these activities and make *Tibeb be Adebabay* your own creative experience!


**A Circus Trip** – Juggling, Trampolines and Hulla Hoops (p.4)
**Do you speak Cinema?** – Direct, shoot and act in your own short film (p.5)
**Rooms and Roads** – Learn about basic principles of architecture (p.6)
**The Urban Suk** – Housing and urban design with reference to "hope" (p.7)
**Foto Quech Quech** – Free photographic portraits and tips and tricks (p.8)
**The Little Creative Center** – Self-expression through portrait drawing (p.9)
**Gamify Addis** – Bring back the fun in the Learning, Loving and Living experience (p.10)
**Music – Be part of It!** – Enjoy music performances or try to play an instrument (p.11)
**Enikmes** – Tasting Arts (p.12)
**Tsehai** – Read with me (p.13)
**Literature** – Let's contribute new ideas! (p.14)


Be part of our **#TibebBeAdebabay** competition and win amazing prizes! Share your best moments on Instagram using **#myTibeb.** Find out more on our channels.

# እንኳን ደህና መጡ

እያንዳንዱ ከተማ ኪነጥበብ እና ባህል ያስፈልገዋል - በጥቂቶች ቅንጦትነት ብቻ ሳይሆን፣ በሁሉም ዜጎቹ መሠረታዊ ፍላጎትነት። በአዲስ አበባ ጉልህ የኪነጥበብ እና የፈጠራ እንቅስቃሴዎች ፍላጎት አለ - ብዙ ታታሪዎችም ታላላቅ ኀሳቦችን ያፈልቃሉ። ሆኖም፣ ብዙ ጊዜ ባህላዊ/ኪናዊ ዝግጅቶች የተመረጡ ጥቂቶች ብቻ የሚታደሙባቸው ነው።

ባለፈው ዓመት፣ የመጀመሪያው ጥበብ በአደባባይ ከ10,000 በላይ ሰዎችን የደረሰ ሲሆን፣ እነርሱም በጥበባቱ ሰላማዊ ክብረበዓል ላይ ታድመዋል - ይኸውም በከያኒዎቹ እና በሌላው ህዝብ መሐል ጥበባዊ መስተጋብር የታየበት ነበር። አሁንም ሁላችሁንም ለሁለተኛው ጥበብ በአደባባይ ስንጋብዛችሁ ከፍተኛ ደስታ ይሰማናል! ኑ እና፣ ከየራሳችሁ የፈጠራ አቅም ጋር ተዋወቁ፣ ከዝነኛ ከያንያን ጋር ተገናኙ እንዲሁም፣ አዳዲስ ነገሮችን ሞክሩ!

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የባህል እና ቱሪዝም ሚኒስትር ላደረገልን ታላቅ ድጋፍ እና ማበረታቻ እናመሰግናለን። የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የባህል እና ቱሪዝም ቢሮ እንዲሁም የየካ፣ ጉለሌ፣ ቦሌ እና ቂርቆስ ክፍለ ከተሞች የባህል እና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች፣ እና የአዲስ አበባ ትራፊክ ማኔጅምንት ቢሮ ይህንን ፕሮጀክት እውን ለማድረግ በሎጂስቲክስ እና በፈቃድ በኩል ከእኛ ጋር በቅርበት ሠርተዋል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ በአዲስ አበባዎቹ ከያኒዎች እና ቡድኖች ጋር በመሥራታችን ኮርተናል። ያለነሱ ትጋት እና አሳቢነት ጥበብ በአደባባይ ሊሳካ አይችልም ነበር።

ተሳተፉ እና ጥበብ በአደባባይን የራሳችሁ የፈጠራ አጋጣሚ አድርጉት!

— ከጎተ ቡድን



From left to right: Dr. Julia Sattler, Yonas Getachew, Tenagne Tadesse, Julia Guenther, Dahna Menner and Brook Getachew. (Photo: Maheder Haileselassie)

በአዲስ አበባ ጎዳናዎች እና የህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች በሚከናወኑት የጥበብ በአደባባይ መስተጋብራዊ ባህላዊ ተግባራት ላይ እንደገና እንሳተፋለን። የባለፈው ዓመት ልምድ በአስደሳች እና አስደናቂ ነገሮች የተሞላ፣ ብዙ የተማርንበትም ነበር። ደግሞም፣ መደሰቻ እና ጊዜ ማሳለፊያ ብቻም አልነበረም፣ ስለአዲስ አበባ የከተማ ህይወት ብዙ መረጃ የተሰበሰበበት እና የተማርንበትም ጭምር እንጂ። ጥበባዊ ክንውኖቹም ጥበብን በባህላዊ ሥፍራዎች ተገኝቶ የማጣጣም ዕድል የሌለው ነገር ግን ጉጉ የሆነ ታዳሚ መኖሩን በግልፅ አሳይተዋል። እንደከያኒዎች እና ዲዛይነሮችነታችን፣ የፈጠራ ሥራዎቻችንን ለብዙኃኑ የከተማው ህዝብ ማጋራት ግዴታችን ነው።

— ፋሲል ጊዮርጊስ

# WELCOME NOTE

Every city needs arts and culture - not just as a luxury for some, but as a necessity for all its citizens. In Addis Abeba, there is a considerable interest in arts and creative activities – and many energetic people come up with great ideas. However, cultural events are often accessible for only a selected few.

Last year, the first edition of Tibeb be Adebabay reached out to more than 10.000 people, who joined into a peaceful celebration of the arts - a creative interaction between artists and the general public. Now, we are very excited to invite you all to the second edition of *Tibeb de Adebabay*! Discover your own creativity, interact with famous artists and try out new things!

We would like to thank the Federal Republic of Ethiopia, the Ministry of Culture and Tourism for its great support and encouragement. And the Culture and Tourism Office of the City Government of Addis Ababa as well as the Culture and Tourism Office of Sub Cities Yeka, Gulele, Bole and Kirkos and the Traffic Management Office Addis Ababa for working closely with us on logistics and permissions and for making this project happen.

Most of all, we are proud to work with such inspiring and engaged artists and groups from Addis Abeba. Without their commitment and passion, *Tibeb be Adebabay* would not be possible. Join in and make *Tibeb be Adebabay* your own creative experience!

— The Goethe Team

Once again, we will experience the interactive cultural activities of *Tibeb be Adebabay* on the streets and public spaces of Addis Abeba. Last years' experience was full of excitement and surprises. The artistic activities demonstrated that there is clearly an eager audience which has no opportunity of experiencing art in a cultural venue. It is our duty, as artists and designers, to share our creative works with the majority of the city dwellers.

— Fasil Giorghis, Co-founder of *Tibeb be Adebabay*

# THE COURAGE TO CHALLENGE ASSUMPTIONS

*Biniam Hailu is an assistant lecturer at the Ethiopian Institute of Architecture, Building Construction and City Development (EiABC) at AAU and initiator of the social studio, a teaching module that tries to push the boundaries of architecture. For Tibeb be Adebabay, he organized a design contest among architecture students to develop and present their ideas on the construction of a mobile Suk that can be used by the artists.*

**GI: How did the idea of an open call for the Tibeb be Adebabay Suks come about?**

BH: In the social studio at EiABC, we try to promote social architecture. The idea is for students to go out and be in touch with their community to identify needs or problems that they can address through architecture and design. So, when I heard about Tibeb be Adebabay, I was very excited about the idea. Surpassing the boundaries of museums or galleries where art is confined and pushing it out to the general public is exactly in sync with our vision to use architecture as a means of engagement and address the underserved majority. The festival has an extensive reach to the community. Honestly, if it had been a project in the social studio, it would have gotten an A.

So, we discussed about a cooperation at Goethe-Institut and came up with the idea of a student competition. Talking to prior participants of Tibeb be Adebabay, we identified some shortcomings of the Suks used last year as well as the potentials. From that, we crystallized the most important requirements for the Suks.

**How was the competition organized?**

When the open call started, we received many applications. It was hard to shortlist them to 24. The students watched a documentary about Tibeb be Adebabay and talked to prior participants and then had time to come up with ideas. We organized a full-day workshop, which was more of a collaborative process than a competition. The students worked together in groups and developed their projects. Most of the 13 ideas presented focused strongly on the functionality of the Suks – being flexible and movable, and not so much on aesthetics. Some others were very iconic and conceptual, so that we did not know if they would be practical as a well. So, we gave the six shortlisted teams another week to further work on the details. At the end, representatives of Goethe-Institut, the social studio and the Tibeb be Adebabay artists looked at the projects and voted for their favorite idea. The one that won is a very iconic structure, it is daring, and that's why people liked it. Now, we are working hard on constructing the Suks in our workshop at EiABC.

**What's the takeaway from this competition for the students and for Tibeb be Adebabay?**

I think it is great for students to get practical experience and to learn from this process. They accompany the whole process, starting from a vague idea, the design and presentation up to the actual construction. It's an example for them to be proactive and projective thinkers.

The great thing working with students is that many of them have the capacity and courage to develop something completely new and challenge assumptions. They are not confined by prior experiences and sometimes this helps in a creative process. That's how they come up with bold ideas. I think Tibeb be Adebabay also benefits from this innovation.

*In July, the social studio will organize an exhibition titled "Architecture for Social Change" at the Goethe-Institut.*

*To find out more about the social studio, find them on Facebook:*

**WWW.FACEBOOK.COM/CHAIROFARCHITECTUREANDDESIGNII/**



Design workshop at Goethe-Institut. (Photo: Dahna Menner)

# ቅቡል ኀሳቦችን የመገዳደር ወኔ

ቢኒያም ኃይሉ በአአዩ የኢትዮጵያ የአርክቴክቸር፣ የግንባታ እና የከተማ ልማት ተቋም ረዳት ሌክቸረር እና የኪነሕንፃን ድንበር ለመግፋት የሚሞክረው የማኅበራዊ ስቱዲዮ (Social studio) ትምህርት ማስተማሪያ ሞጁል ጠንሳሽ ነው፡፡ በጥበብ በአደባባይ በአርኪቴክቸር ተማሪዎች መካከል የዲዛይን ውድድር አካሂዶ፣ ከያኒያኑ ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸውን ተንቀሳቃሽ ሱቆች መገንባት የሚያስችሉ ሐሳቦችን አመንጭተው እንዲያቀርቡ አድርጓል።

### ለጥበብ በአደባባይ ሱቆች ግልፅ ጥሪ የማቅረቡ ኀሳብ እንዴት መጣላችሁ?

በተቋማችን ማኅበራዊ ስቱዲዮ፣ ማኅበራዊ ኪነሕንፃን ለማስተዋወቅ እንሞክራለን። ኀሳቡ፣ ተማሪዎች ከማኅበረሰቡ ጋር በመቀራረብ በአርኪቴክቸር እና ዲዛይን አማካይነት እነርሱ ሊያሟሏቸው ወይም ሊፈቷቸው የሚችሏቸውን ፍላጎቶች ወይም ችግሮች እንዲለዩ ማድረግ ነው። ስለዚህ፣ ስለ ጥበብ በአደባባይ ስሰማ፣ በኀሳቡ በጣም ተደሰትኩ። ስነጥበብ የታገተባቸውን ሙዚየሞች እና ጋለሪዎች አልፎ፣ ጥበብን ወደ ሕዝብ ገፍቶ ማውጣት፣ በቂ አገልግሎት የማያገኘውን ሕዝብ በኪነሕንፃ አማካይነት ለመድረስ ከያዝነው ርዕይ ጋር በትክክል የሚቀናጅ ነው። ፌስቲቫሉ ለማህበረሰቡ ሰፊ ተደራሽነት አለው። እውነቱን ለመናገር፣ ለሶሻል ስቱዲዮ የቀረበ ፕሮጀክት ቢሆን ኖሮ "A" ያስገኝ ነበር።

ከዚያ፣ ከጎተ ኢንስቲቲዩት ጋር ተባብሮ ለመሥራት ተወያየን እና የተማሪዎች ውድድር ኀሳቡ መጣ። ከቀድሞዎቹ የጥበብ በአደባባይ ተሳታፊዎች ጋር በመነጋገር፣ የአምናዎቹን ሱቆች ጉድለቶች እና ልንጠቀምባቸው የምንችላቸውን በጎ ጎኖቻቸውን ለየን። ከዚህ በመነሳት ለሱቆቹ በጣም የሚያስፈልጉትን ነገሮች ጥርት አድርገን አስቀመጥን።

### ውድድሩ እንዴት ተካሄደ?

የውድድር ጥሪው ይፋ እንደሆነ፣ ብዙ አመልካቾችን ተቀበልን። ከእነርሱ መካከል 24 መርጦ ማስቀረት ከባድ ነበር። ተማሪዎቹ ስለ ጥበብ በአደባባይ የተዘጋጀውን ዘጋቢ ፊልም አይተው ከአምና ተሳታፊዎች ጋር ከተነጋገሩ በኋላ፣ ኀሳቦች የሚያፈልቁበት ጊዜ ተሰጣቸው። ከውድድሩ በላይ እርስ በርስ የተቀራረብንበትን የሙሉ ቀን ወርክሾፕ አካሔድን። ተማሪዎቹ ተቧድነው፣ ኀሳቦቻቸውን አዳበሩ፡፡ ከ13ኡ ኀሳቦች አብዛኞቹ በሱቆቹ ተግባራዊነት ላይ - ማለትም ለአጠቃቀም የሚመቹ እና ተንቀሳቃሽ መሆናቸው ላይ እንጂ ውበታቸው ላይ ያን ያህልም ያተኮሩ አልነበሩም፡፡ ጥቂቶቹ ደግሞ ተምሳሌታዊ እና ኀሳባዊ ከመሆናቸው የተነሳ ተግባራዊ ሊደረጉ መቻላቸውን እርግጠኞች አልነበርንም። ስለዚህ ተለይተው ለተመረጡት ስድስት ቡድኖች በዝርዝሩ ላይ እንዲሠሩ ሌላ አንድ ሳምንት ሰጠናቸው። በመጨረሻ የጎተ ኢንስቲቲዩት ተወካዮች፣ ሶሻል ስቱዲዮ እና የጥበብ በአደባባይ አርቲስቶች ፕሮጀክቶቹን ተመልክተው ለመረጡት ኀሳብ ድምፅ ሰጡ፡፡ ያሸነፈው ኀሳብ ተምሳሌታዊ ቅርፅ ነው፣ ደፋርም፣ ደግሞ ለዚህም ነው ሰዎች የወደዱት። አሁን፣ በሕንፃ ኮሌጅ ወርክሾፓችን ሱቆቹን በትጋት እየገነባን ነው።

### ከዚህ ውድድር ተማሪዎቹ እና ጥበብ በአደባባይ ምን ጥቅም ያገኛሉ?

ተማሪዎቹ ተግባራዊ ልምድ የሚቀስሙበት አጋጣሚ ማግኘታቸው እና ከሒደቱም መማራቸው ትልቅ ነገር ነው። ካልጠራው ኀሳብ ጀምሮ፣ ዲዛይኑን ከማውጣት እና ከማቅረብ እስከ ግንባታው ድረስ በሙሉ ሒደቱ ተሳትፈዋል። ይሄ ለእነሱ ተግባራዊ እና ፅንሰ ኀሳባዊ አሳቢዎች የሚሆኑበት ምሳሌያቸው ነው።

ከተማሪዎች ጋር የመሥራት ትልቁ ነገር፣ ብዙዎቹ ሙሉ በሙሉ አዲስ ኀሳብ የማመንጨት እና ቅቡል ኀሳቦችን የመገዳደር አቅም እና ድፍረት ያላቸው መሆናቸው ነው። በቀደሙ ልምዶቻቸው አይታጠሩም፣ ይህም አንዳንድ ጊዜ የፈጠራ ሂደትን ያግዛል። በዚህ መንገድ ነው የሚተገበሩ የማይመስሉ እና ደፋር ኀሳቦችን የሚያፈልቁት። ጥበብ በአደባባይም በዚህ ፈጠራ የሚጠቀም ይመስለኛል።


መረጃ፡- ሐምሌ ውስጥ፣ ሶሻል ስቱዲዮ "አርኪቴክቸር ለማኅበራዊ ለውጥ" የሚል አውደ ርዕይ በጎተ ኢንስቲቲዩት ለማካሔድ እየተዘጋጀ ነው።

ስለሶሻል ስቱዲዮው የበለጠ ለመረዳት፣ ይህንን የፌስቡክ ገፁን ይጎብኙ፡-

**WWW.FACEBOOK.COM/CHAIROFARCHITECTUREANDDESIGNII/**



Prototype of winning design. (Photo: Biniam Hailu)



CAD Drawings of winning design.

# የሱቅ ንድፍ ስራ ውድድር

ተስፋ የሚጣልባቸው የኪነሕንፃ ተማሪዎች የሱቅ ዲዛይን ፈጠራዎቻቸውን በማቅረብ ውድድሩ ላይ ተሳትፈዋል።

አሸናፊዎቹ፡-

1ኛ አዜብ ግዛቸው እና ኢየሩሳሌም ጥበበ

2ኛ ሚልኬሳ አበራ እና ናትናኤል መኮንን

3ኛ ሮዳስ ሙሉጌታ እና ሳራ ተረፈ

# THE DESIGN CHALLENGE

With their creative designs, aspiring architecture students participated in the Contest.

The winners are:

1st Azeb Gizachew and Eyerusalem Tibebe

2nd Milkesa Abera and Natnael Mekonen

3rd Rodas Mulugeta and Sara Terefe

> ውድድሩ ከአካዴሚያዊው ውጭ ያለውን ሌላ የኪነሕንፃ ገፅታ የምናይበትን ዕድል ሰጥቶናል።
>
> — ናትናኤል መኮንን

> When I saw the vision and the aim of Tibeb be Adebabay, it was interesting for me, because it's social and interactive. It gives us the opportunity to communicate directly with the public. A challenge was to accommodate the needs of all artist groups and their performances. The structure is adjustable in height and form. Our idea was to involve the public as much as possible. That's why we made the Suk transparent.
>
> – Eyerusalem Tibebe

> ዲዛይኑ ለሕዝብ ዕይታ ሊቀርብ በመሆኑ ኩራት ተሰምቶኛል። ደስ የሚሉ ሰዎችን ያገኘንበት ትልቅ አጋጣሚ ነበር። ከዚህ ፌስቲቫል ትምህርት ወስደን እና የዲዛይናችንን ጉድለቶች ተመልክተን፣ ለወደፊቱ ዳግም ጥቅም ላይ እንዲውል ዲዛይናችንን አሻሽለን እንደምንሠራው ተስፋ አለኝ።
>
> — አዜብ ግዛቸው

# የሰርከስ ጉዞ

| ሰርከስ |
| --- |
| 28 ሚያዝያ (እሑድ): ብሔራዊ ትያትር |
| 2  ግንቦት (ሐሙስ): መስቀል አደባባይ |



**ፕሮግራሙ**

ምንም እንኳን ጎዳናዎች ለሰርከስ ትርዒቶች ተስማሚ ቦታዎች ቢሆኑም፣ በአሁኑ በእንቅስቃሴ በተሞላ ዓለም ግን፣ የሰርከስ ከያኒያን አደባባይ ላይ ትርዒታቸውን የሚያሳዩበት ዕድል ካለመኖር የሚቆጠር ነው። በጥበብ በአደባባይ፣ ዝነኛው የአዲስ አበባው ፍካት ሰርከስ ልዩ እና ኮንቴምፖራሪ የሰርከስ ትርዒት ለማሳየት፣ ትላልቅ ትራምፖሊኖችን፣ ጀግሊንግ ፒኖችን፣ ሁላ ሁፖችን እና ሌሎች መሣሪያዎቹን ይዞ ወደ ከተማዋ አደባባዮች ይወጣል። ጎብኚዎች በተመልካችነት ሳይገደቡ ዝላይን እና ጀግሊንግን የመሳሰሉ ክዋኔዎችን ይሞክራሉ። ኪናዊ ሙከራዎቻቸውም ተቀርፀው በጎተ ኢንስቲቲዩቱ የመዝጊያ ሥነስርዓት ላይ ለዕይታ ይቀርባሉ።

**አዘጋጆቹ**

ፍካት ሰርከስ ለሰርከስ ጥልቅ ፍቅር ባላቸው ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች በ2004 አዲስ አበባ ውስጥ ተጀመረ። ወጣቶቹ የሚጋባ ኃይላቸውን ከመድረክ ወደተመልካች ማሰራጨት የሚችል የወጣቶች ሰርከስ ቡድን የመፍጠር የጋራ ህልም ነበራቸው። አሁን ሰርከስ ፍካት በአገር ውስጥ እና በዓለማቀፍ ደረጃ የሚሠሩ 30 የሰርከስ አርቲስቶች አሉት። የሙያ ብቃታቸውን የጠበቁ ትርዒቶችን መድረክ ላይ ከማቅረብ በተጨማሪ፣ ፍካት ሰርከስ ፒያሳ በሚገኘው ትምህርት ቤቱ አማካይነት እና፣ በህፃናት ማሳደጊያዎች እና በግል ትምህርት ቤቶች በሚያካሂዳቸው ፕሮጀክቶች እና በሌሎችም ፕሮግራሞቹ አማካይነት የሰርከስን ጥበብ በመዲናችን ለማስፋፋት ይተጋል። ከ2009 ጀምሮ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የህፃናት ክፍል ፈገግታ መድሃኒት ነው የተባለውን ዕለታዊ የመዝናኛ ዝግጅቱን እያካሔደ ይገኛል። የህፃናት ታካሚዎቹን ስሜታዊ እና ስነልቡናዊ ደህንነት ለማሻሻል፣ ወዲያውም የተሻለ የጤና ሁኔታን ለማንቃት፣ ፍካት ሰርከስ በኢትዮጵያ ትልቁ ሆስፒታል ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ክላውን ዶክተሮችን (ሐኪም መሳይ አጫዋቾችን) እና አኒሜተሮችን አምጥቷል።

ከቅርብ ጊዜዎቹ የፍካት ሰርከስ ፕሮጀክቶች አንዱ፣ በየወሩ የመጨረሻ የሰንበት ቀናት የምናካሂደው "ወርሃዊ ትርዒት" ነው። ፍካት ሰርከስ በ2015 የአፍሪካ ሰርከስ ጥበባት ፌስቲቫልን በማነሳሳት እና በማስተባበር በአፍሪካዊ ሰርከስ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ሁለተኛው ፌስቲቫል ባሳለፍነው መጋቢት፣ አዲስ አበባ ላይ ተካሂዷል።


**WWW.FEKATCIRCUS.COM**



ምንም እንኳን ጎዳናዎች ለሰርከስ ትርዒቶች ተስማሚ ቦታዎች ቢሆኑም፣ በአሁኑ በእንቅስቃሴ በተሞላ ዓለም ግን፣ የሰርከስ ከያኒያን አደባባይ ላይ ትርዒታቸውን የሚያሳዩበት ዕድል ካለመኖር የሚቆጠር ነው።

# A CIRCUS TRIP

| Circus |
| --- |
| 6 May (SUN): National Theater |
| 10 May (THU): Meskel Square |



**THE PROGRAMME**


Although streets are the natural habitat of circus art, in today's traffic populated world circus artists rarely get the opportunity to perform in the open. For Tibeb be Adebabay, Addis Abeba's famous Fekat Circus will take big trampolines, juggling pins, hulla hoops and other equipment to the public squares of the city for a unique and contemporary circus experience! Visitors can not only watch the artists perform but also participate in workshops and try jumping and juggling themselves. Your artistic experiments will be documented and screened at the final exhibition at the Goethe-Institut.

**THE CURATORS**

Fekat Circus, "blossoming" circus in Amharic, was started in 2004 in the outskirts of Addis Abeba, by a group of young Ethiopians united by a deep passion for circus. They shared a common dream – to create a circus of youngsters who spread their infectious energies from stage. Today Fekat circus comprises of 30 professional artists who perform in Ethiopia and internationally. Besides staging professional shows, Fekat Circus spreads the circus arts in the capital through its school in Piassa and outreach programs in orphanages, private schools and events. Since 2009, Fekat Circus provides daily entertainment activities at the pediatric ward of the Black Lion Hospital through its initiative called "Smile Medicine". For the first time, Fekat circus brought clown doctors and animators inside the largest public hospital in Ethiopia with the aim to improve the emotional and psychological well-being of its young patients, and consequently stimulate better health conditions.

One of the latest Fekat Circus projects is the "Monthly show", which happens on the last weekend of each month. Fekat Circus also plays an important role in the African circus scene by initiating and organizing the African Circus Arts Festival in 2015. The second edition of the Festival took place in March 2018 in Addis Abeba.

**WWW.FEKATCIRCUS.COM**



All photos: Fekat Circus

# ሲኒማኛ ይናገራሉ?

| ፊልም |
|---|
| 26 ሚያዝያ (ዓርብ): መስቀል አደባባይ |
| 27 ሚያዝያ (ቅዳሜ): መስቀል አደባባይ |
| 28 ሚያዝያ (እሑድ): ቦሌ መድኃኔአለም |
| 29 ሚያዝያ (ሰኞ): ቦሌ መድኃኔአለም |


Hiwot Admasu (Photo: Behailu Shiferaw)

**ፕሮግራሙ**

ሲኒማ ድንበሮችንም፣ ባህሎችንም የሚሻገር ቋንቋ ነው። በብልሃት ከተጠቀሙበት፣ ብዙኃኑን ሕዝብ የሚማርክ እና ማኅበረሰብን መልክ ለማስያዝ አቅም ያለው የኪነጥበብ ቅርፅ ነው። በኢትዮጵያ፣ ያልተነገሩ ታሪኮች፣ ያልታወቁ ቦታዎች፣ የበለጸገ ባህል እና በራሱ ቋንቋ የሚቀርቡለትን ፊልሞች የሚወድ በጣም ጉጉ ተመልካች ሞልቶናል። የሀገር ውስጡ የፊልም ኢንዱስትሪ የሲኒማ ባህልን ለመፍጠር እየታገለ ቢሆንም፣ ገና ብዙ የሚቀረው ሥራ አለ። የፊልም ትምህርት ቤቶች እና የተለያዩ ዐይነት ፊልሞችን የሚያሳዩ ሲኒማ ቤቶች ይጎድላሉ። በተጨማሪም፣ አዲስ አበባ፣ ከሌሎች የውጭ ከተሞች በተቃራኒ፣ ምንም ዐይነት የፊልም ክብረ በዓል የላትም። በዚህ ሱቅ አማካይነት፣ ለጉጉ ጎብኚዎቻችን ቤተ ኪነጥበባትን/ የዓለም ሲኒማን እያስተዋወቅን፣ ይህንን የጎደለንን የፊልም ክብረ በዓል መፍጠር እንፈልጋለን።

ፕሮግራሙ ሦስት ጉዳዮችን ያካትታል፦ ፊልም መሥራት፣ ተዋናይ መረጣ እና ፊልሞች ማሳየትን። ጎብኚዎች በሱቁ ዙሪያ ሊሠሩ የሚችሉ የአጭር-አጭር ፊልሞችን መምራት (ዳይሬክት ማድረግ)፣ መቅረፅ እና መተወን ይችላሉ። ካሜራ እና የድምፅ መሣሪያ እናቀርባለን፣ ፊልሞቹን ኤዲት እናደርጋለን፣ በማግሥቱ በቲቪ በማሳየት ለተሳታፊዎች እናቀርባለን። ተስፋ የሚጣልባቸውን ወጣት የፊልም ሠሪዎች እናማክራለን። በተጨማሪም፣ የመተወን ፍላጎት ያላቸውን ተሳታፊዎች ፎቶ አንስተን፣ ዝርዝር መረጃዎቻቸውን ተዋናይ ለሚመርጡ ወኪል ድርጅቶች እና ለሌሎች የፕሮዳክሽን ኩባንያዎች እናቀብላለን። ከዚህም በላይ፣ የአጫጭር ፊልሞች ትርዒት፣ ለፊልሞች የሚሆኑ ጥቆማዎች እና ስለ ሲኒማ እና ስለ ፊልም አሠራር የሚናገሩ መጻሕፍት፣ እንዲሁም በጣም በርካታ ብሉያት ፊልሞች በሱቁ ውስጥ ይኖራሉ። ተሳታፊዎች በጀርመን የባህል ተቋም የሲን-ክለብ አባል እንዲሆኑ እና በሴንቸሪ ሲንፕሌክስ በወር አንዴ በሚደረገው “አዲስ ኢንዲ ሲኒማ ስክሪኒንግ” (“አዲስ ነጻ የፊልም ማሳያ”) ፕሮግራም ላይ እንዲገኙ ይጋበዛሉ። ሁለቱም ፕሮግራሞች ወጣት ፊልም ሠሪዎችን ለማገዝ እና የጠቅላላውን የፊልም አፍቃሪ ስሜት ለመኮርኮር ታስበባቸው የተነደፉ ናቸው።

**አዘጋጆቹ**

ህይወት አድማሱ ጌታነህ ለሽልማት የበቃች፣ ፊልሞችን ዳይሬክት የምታደርግ እና የምትደርስ ፊልም ሠሪ ናት። የፊልም ሠሪነት ፍላጎት ያደረባት በከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኤሌክትሪካል ምህንድስና ከተመረቀች በኋላ ነበር። “ኢንዲ” ወይም “አርት ሀውስ” የሚባለውን የሲኒማ ዘውግ በብሉ ናይል የፊልም እና የቴሌቪዥን አካዴሚ ተዋወቀች፡ ፡ ከዚያ ወዲህም፣ በበርሊን፣ በቶሮንቶ፣ በካንስ፣ በደርባን፣ በሎካርኖ፣ በሉክሶር እና በሌሎችም ሥፍራዎች በርካታ ወርክሾፖችን እና ስልጠናዎችን ተካፍላለች። የመጀመሪያ አጭር ፊልሟ “አዳዲስ ዐይኖች” (“New Eyes”) ቀድሞ የታየው በተከበረው የቬኒስ ፊልም ፌስቲቫል ላይ ነበር። ከዚያ በኋላም በቶሮንቶ፣ ሮተርዳም፣ ሲያትል እና ደርባን፣ እንዲሁም በሌሎች የአውሮፓ፣ የአፍሪካ እና የዩናይትድ ስቴትስ ከተሞች ውስጥ በተካሄዱ የፊልም ፌስቲቫሎች ላይ ታይቶላታል። ህይወት አሁን፣ የመጀመሪያ የሙሉ ሰዓት ፊልሟን እየሠራች ትገኛለች።


The film suk 2017 (Photo: Julia Guenther)

ሔኖክ መብራቱ በአዲስ አበባ ተወልዶ ያደገ፣ ሙያውን ራሱን ያስተማረ ፊልም ሠሪ ነው። የኮምፒውተር ሳይንስ ትምህርቱ የግራፊክ ዲዛይንን፣ የኮምፒውተር አኒሜሽንን እና የጌም ፍጠራን ዓለም አስተዋውቆታል። ለዓመታት ወዲህ ወዲያ ካለ በኋላ፣ ሄኖክ ለተረክ ተራኪነት እና ለመምህርነት ያለውን ፅኑ ፍላጎት ተረዳ። ሔኖክ በመቶዎች በሚቆጠሩ የቲቪ እና የራዲዮ ማስታወቂያዎች፣ በደርዘን ዘጋቢ ፊልሞች ላይ፣ በአንድ ሁለት የቲቪ ትርዒቶች እና በአምስት የሙሉ ሰዓት ፊልሞች ላይ ሠርቷል። ባለፉት 17 ዓመታት የአኒሜተርነት፣ የድሮን ኦፕሬተርነት፣ የዳይሬክተርነት፣ የኤዲተርነት፣ የግራፊክ ዲዛይነርነት፣ የፎቶግራፈርነት፣ የፕሮዲዩሰርነት፣ የቪዡዋል ኢፌክትስ ሱፐርቫይዘርነት፣ የዌብ ዴቬሎፐርነት እና የደራሲነትን ጨምሮ የብዙ ሙያ መለዮዎችን ለብሷል። አሁን በአክሽን ሚዲያ በደራሲነት፣ በዳይሬክተርነት፣ በፕሮዲዩሰርነት እና በቪዡዋል ኢፌክትስ ሱፐርቫይዘርነት እያገለገለ ነው።

**WWW.HENOKMEBRATU.COM**

> ሲኒማ ድንበሮችንም፣ ባህሎችንም የሚሻገር ቋንቋ ነው።

# DO YOU SPEAK CINEMA?

| Film |
|---|
| 4 May (FRI): Meskel Square |
| 5 May (SAT): Meskel Square |
| 6 May (SUN): Bole Medhanialem |
| 7 May (MON): Bole Medhanialem |

**THE PROGRAMME**

Cinema is a language that crosses borders and cultures. It's an art form that is appealing for the masses and a powerful tool to shape a society if wisely used. In Ethiopia, we are blessed with untold stories, undiscovered locations, a rich culture and a very curious audience that loves movies in its own language. Though the local film industry is thriving to create a cinema culture, still, there is a lot to be done. Film schools and cinemas that show a variety of films are missing. In addition, there is almost no celebration of cinema in Addis Abeba unlike other cities abroad. Through our programme, we want to create such a celebration of movies while introducing art house/ world cinema for the curious visitors.

The programme consists of three aspects: filmmaking, casting, and movies. Visitors are able to direct, shoot and act on super short films that can be made around the Suk. We offer camera and sound gear, edit the films, screen them on a TV the next day and make them available for the participants. We also give advice for young aspiring filmmakers. Furthermore, we take pictures of visitors who are interested in acting and pass their contact details to casting agencies and other production companies. Last but not least, there are screenings of short films, recommendations for movies and books about cinema and filmmaking as well as a number of classical films available at the Suk. Participants are invited to be a member of the Cine-club at the Goethe Institute and attend the once a month program 'Addis Indie Cinema Screening' at the Century Cineplex. Both programmes are designed to support young filmmakers and inspire the general cinema lovers in the country.


The film suk 2017 (Photo: Julia Guenther)

**THE CURATORS**

Hiwot Admasu Getaneh is an award winning independent filmmaker who directs and writes films. She started her passion of making movies after studying Electrical and Computer Engineering at Addis Ababa University. She was introduced to indie or art house cinema at the Blue Nile Film and Television Academy. Afterwards, she attended a number of workshops and trainings in Berlin, Toronto, Cannes, Durban, Locarno, Luxor and other places around the world. Her first short film "New Eyes", premiered in the prestigious Venice Film Festival. It was also shown at international film festivals in Toronto, Rotterdam, Seattle and Durban, among others in Europe, Africa and the US. Currently, Hiwot is working on her first feature film.

Henok Mebratu is a self-taught filmmaker born and raised in Addis Abeba. His background is computer science, which introduced him to the world of graphic design, computer animation and game development. After years of jumping around, Henok found his passion in story-telling and teaching. Henok has worked on hundreds of TV and Radio commercials, a dozen documentaries, a couple of TV Shows and 5 feature films. In the past 17 years, he wore many hats as an animator, drone operator, director, editor, graphic designer, photographer, producer, visual effects supervisor, web developer and a writer. Currently, he is mainly serving as a writer, director, producer and visual effects supervisor at Action Media.


Henok Mebratu (Photo: Action Media)

**WWW.HENOKMEBRATU.COM**

# ጓዳ እና ጎዳና

**ኪነ-ህንጻ**

26 ሚያዝያ (ዓርብ): ቦሌ መድኃኔአለም

27 ሚያዝያ (ቅዳሜ): ብሔራዊ ትያትር

1 ግንቦት (ረቡዕ): ስድስት ኪሎ

### ፕሮግራሙ

የአዲስ አበባ የከተማ ቦታዎች የነዋሪዎቹን ታሪክ እና ባህል ከተለያዩ የማንኛውም ከተማ ችግሮች ጋር አጣምረው ያሳያሉ። የመዲናዋን በጎ ገፅታዎች እና ችግሮች ለመድረስ፣ ወደ ከተማ ንድፍ ከመግባታችን በፊት፣ ከህዝቡ ጋ በምንፈጥራቸው መስተጋብሮች አማካይነት ለይተን ልናውቃቸው እና ልንመረምራቸው ይገባል። የኪነሕንፃ መሠረታዊ መርሆች፣ በቀላል የንድፎች እና የናሙና ሥራ ልምምዶች አማካይነት የፈጠራ ችሎታዎች የሚጎለብቱበትን ዕድል ይሰጣሉ። የቅርፅ፣ የቦታ፣ እና የአደራደር መሠረታዊ ሐሳቦች፣ ሥምረትን፣ ውበትን እና ፅኑነትን የማምጣት ግብ ባለው የማንኛውም ፊዚካዊ አካል የዲዛይን ሥራ ውስጥ በተግባር ሊውሉ ይገባል።

ሱቁ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የከተማ ህይወታቸውን እንዲገልፁ ያሳትፋል፤ እንዲሁም ስለ ኪነሕንፃ እና የከተማ ዲዛይን መሠረታዊ ትምህርቶችን በመስጠትም የፈጠራ ችሎታቸውን ያነቃቃል። ጎብኚዎች ከአዘጋጆቹ እና ከሌሎች የእነሱን መሰል ፍላጎት ካላቸው ጎብኚዎች ጋ በመሆን የኪነሕንፃ መሠረታዊ መርሆዎችን ያሳያሉ። ከዚያም ባሻገር፣ ሱቁ ለደንበኞች የኪነ ህንፃን መሠረታዊ መርሆች የሚያሳዩ፣ ትዕይንታዊ መመሪያዎች ከመስጠት እና ከ“ኪዩቢስት“ ሥልጠና ጎን ለጎን፣ የፈጠራ ልምምድ ማድረጊያ ዕድልም ያመቻቻል። የሁሉም ተሳታፊዎች የመጨረሻ ፈጠራ ሥራዎች ፎቶግራፍ ተነስተው፣ ለዕይታ ይቀርባሉ። ከዚያ በኋላም፣ ይሄ ስብስብ ጎተ ኢንስቲቲዩት ውስጥ በአውደ ርዕይ ቀርቦ ውይይት ይደረግበትና ይቋጫል።



Discussing the principles of architecture (Photo: Behailu Shiferaw)

### አዘጋጁ

ሱቁ በኢትዮጵያ የአርክቴክቸር፣ የግንባታ እና የከተማ ልማት ተቋም፣ ተማሪዎች የሚመራ ነው። ተቋሙ “ዲዛይን እና ዘላቂነት“ በሚል ርዕስ ሥር፣ በአርክቴክቸር፣ በዲዛይን፣ በግንባታ፣ በከተሜነት፣ በአካባቢ ጥበቃ ዕቅድ፣ በማኔጅመንት እና በቴክኖሎጂ መስኮች፣ የኢንዱስትሪዎችን ዕድገት፣ አቅም እና ተወዳዳሪነት የሚያበረታታ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው። ግባቸውም በግንባታው ዘርፍ ኢትዮጵያ ላሏት እንደ የመኖሪያ ቤት እና የመሠረተ ልማት አቅርቦት ላሉ ፍላጎቶች ምላሽ መስጠት ነው።

### የቡድኑ አባላት

አንተነህ ጌታቸው፣ በእምነት ደምሴ፣ ዳዊት ጉዲሳ፣ ኤልናታን ማቴዎስ፣ እስክንድር ፈቃደ፣ ኢዮስያስ ተክሌ፣ እዝራ አለምሰገድ፣ ቅዱስ ዮሐንስ፣ ማህሌት ረታ፣ ናታን መብራቴ፣ ሩቢ ታዬ፣ ሳሌም ካሳ፣ ትዕግስት ዘላለም፣ ያስሚን አብዱ፣ ያሬድ አዳም ናቸው።

**WWW.EIABC.EDU.ET**



EiABC's suk 2017 (Photo: Bemnet Demissie)

> ሱቁ ስለ ኪነሕንፃ እና የከተማ ዲዛይን መሠረታዊ ትምህርቶችን በመስጠትም የፈጠራ ችሎታቸውን ያነቃቃል።

# ROOMS AND ROADS

**Architecture**

4 May (FRI): Bole Medhanialem

5 May (SAT): National Theater

9 May (WED): Sedist Kilo

### THE PROGRAMME

The urban spaces of Addis Abeba project the history and culture of its dwellers in combination with various problems any city faces. To address the qualities and the problems projected in the capital, we need to discover and research them through interactions with the public before proceeding to urban design. The fundamental principles of architecture provide the opportunity to develop creative capabilities through simple drawing and model making exercises. The basic ideas of Form, Space and Order must be applied to the design of any physical object for the purpose of creating harmony, beauty and firmness.

The Suk invites the urban dwellers of Addis to express their urban life and to stimulate their creativity by offering basic teachings of architecture and urban design. Visitors get the chance to interact with the curators and other visitors with similar interest in fundamental principles of architecture. Furthermore, the Suk offers creative exercises along with visual guidelines that show the participants the fundamental principles of architecture. The final creations will be photographed and displayed. Afterwards, this collection will be exhibited for further discussions and conclusions at the Goethe-Institut.

### THE CURATORS

The Suk is curated by students of the Ethiopian Institute for Architecture, Building Construction and City Development (EiABC). EiABC is a think-tank that fosters the development, capacity and competitiveness of industries in the field of Architecture, Design, Construction, Urbanism, Environmental Planning, Management and Technology under the headline “Design and Sustainability”. Their goal is to react to actual needs of Ethiopia in the building sector like the provision of housing and infrastructure.



Locating favorite places in Addis Abeba (Photo: Behailu Shiferaw)

### TEAM MEMBERS

Anteneh Getachew, Bemnet Demissie, Dawit Gudisa, Elnathan Matheos, Eskinder Fekade, Eyosias Tekle, Ezra Alemseged, Kidus Yohannes, Mahlet Retta, Natan Mebrate, Ruby Taye, Salem Kassa, Tigist Zelalem Yasmin Abdu, Yared Adam.

**WWW.EIABC.EDU.ET**

Be part of our
**#TibebBeAdebabay**
competition and win amazing prizes!

Share your best moments on Instagram using
**#myTibeb**

Find out more on our channels

# የ40/60 ቤቶች ምናባዊ ተስፋ

| ከተማ ዲዛይን |
|---|
| 27 ሚያዝያ (ቅዳሜ): መገናኛ |
| 28 ሚያዝያ (እሑድ): ብሔራዊ ትያትር |
| 29 ሚያዝያ (ሰኞ): ቦሌ መድኃኔአለም |
| 2 ግንቦት (ሐሙስ): መስቀል አደባባይ |

**ፕሮግራሙ**

ሱቁ በ"ተስፋ" ማንፀሪያነት፣ ዲጂታል መሣሪያዎችን በመጠቀም ቤቶች እና ከተማ-ነክ አርእስተ ጉዳዮችን ያቀርባል። ይህ ሙከርት ዲጂታል ዕድሎች ተስፋን በመስጠት ረገድ እንዴት ያሉ ሚናዎችን እንደሚጫወቱ ለመፈተሽ የታለመ ነው።

ሱቁ ሦስት የከተማ ተግባራትን ያቀርባል፦

**እነሆ መኖሪያዎት**

የ40/60 ቤቶች መስተጋብራዊ "ቨርቹዋል" ትርዒት

ቤት ከሰው ልጆች መሠረታዊ ፍላጎቶች አንዱ እና ከአዲስ አበባ ዓበይት የከተማ ተግዳሮቶችም አንዱ ነው። በመንግሥት እና በግል ኩባንያዎች የተለያዩ ጥረቶች እና መርሐ ግብሮች ተተግብረዋል። ሁሉም ለማለት በሚያስደፍር ደረጃ፣ የቤቶች ፕሮጀክቶቹ ዘግይተዋል፣ የተጠናቀቁትም ቢሆን በዝቅተኛ የጥራት ደረጃ የተገነቡ ናቸው።

በአዲስ አበባ፣ በጣም ከታወቁት እና ብዙ ከተወራላቸው የቤቶች ፕሮጀክቶች አንዱ የ40/60 የቤቶች ግንባታ መርሐግብር ሲሆን፣ ግንባታው ከመዘግየቱም በላይ በገዢዎቹ ላይ ወጪዎችን ጨምሮባቸዋል። ከብዙ ሺህ ተመዝጋቢዎች መሐል፣ ያውም ሙሉ ክፍያውን አስቀድመው ካጠናቀቁት መሐል፣ ጥቂት ሺህዎች ዕጣ ወጥቶላቸው ለመጠናቀቅ የተቃረቡትን ቤቶች ተረክበዋል።

ከዚህ አኳያ፣ እኛ የከተማ ሱቃችንን በመጠቀም፣ የመረጥናቸውን ሁለት የ40/60 ቤቶች ምሳሌዎች ሰዎች በቅርበት ሊያስተውሉት ወደሚችል ቨርቹዋል እውነታነት ቀይረን፣ በአፓርትመንት መኖር ምን ስሜት እንደሚፈጥር እናሳያለን። የሚመለከተው የመንግሥት አካል እና የመርሐግብሮቹ ንድፍ አውጭዎች ወደፊት ሌሎች መርሐ ግብሮችን ሲያቅዱ እንዲያስቡባቸው ከተሳታፊዎች የሚቀርቡ አስተያየቶችንም ሰብስበን እንሰጣቸዋለን።



Measuring heights at last year's urban suk (Photo: Behailu Shiferaw)

**"ዲጂታል ጉዞ ወደተመረጡ ቦታዎች" - ሊያዩዋቸው ወደሚገቡ ሥፍራዎች የሚደረጉ መስተጋብራዊ "ቨርቹዋል" ጉዞዎች**

ወደ ሌሎች አገሮች መጓዝ፣ ለተርታው አዲስ አበቤ በጣም ውድ እና አስቸጋሪ ተግባር ነው። ሰዎችን ወደር የለሽ ከተሰኙት እና ከታዋቂዎቹ ሥፍራዎች እና ሕንፃዎች ወደአንዳንዶቹ፣ በኮምፒውተር አማካይነት አስጉዘን፣ የሌሎች ከተሞችን የከተማ ህይወት እና ኪነሕንፃ እንዲመለከቱ እናደርጋለን።

ለመቀረፅ ፈቃደኛ የሆኑ ታዳሚዎች፣ ስለ"ቨርቹዋል" ጉዟቸው የተሰሟቸው ስሜቶች በምስል ተቀርፀው በጎተ-ኢንስቲቲዩት በሚደረገው የመዝጊያ አውደ ርዕይ ላይ ይቀርባሉ።

**"ዘንድሮም እንደ አምና - ራስዎን ያነፃፅሩ" - የአምናው ሱቅ ዲጂታል**

የአምናዎቹ "የከተማ ሱቅ" ሙከርቶች ማለት "የእርስዎ ከተማ ናት - ይገንቧት" እና "ምን ያህል ረጅም ኖት?" የትንተና ውጤቶች ለዕይታ ይቀርባሉ። ተሳታፊዎች ራሳቸውን ከውጤቶቹ ጋር እንዲያነፃፅሩ ለማበረታታት፣ የተሳታፊዎች አማካይ ቁመት እና ለቅኝቶች የተሰጡ ዋና ዋና ምላሾች ይቀርባሉ።

**አዘጋጁ**

ማኀደር ገብረመድኅን ቦርጋ፣ በተለይ በአርኪቴክቸር፣ በኢንቴሪየር ዲዛይን እና በግንባታ ላይ በሚሠራው እና በመስከረም 2001 ዓ.ም. በተቋቋመው "የማ አርኪቴክቸር ፒኤልሲ" የማማከር እና የግንባታ ድርጅት፣ ዋና አርኪቴክት እና ሥራ አስኪያጅ ነው። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኪነሕንፃ እና በከተማ ማቀድ በ1991 ዓ.ም. ከተመረቀ ወዲህ፣ ከግል ትላልቅ ቤቶች እስከ ሆስፒታሎች እና ከኢንዱስትሪ ሕንፃ እስከ የመዝናኛ እና የትምህርት ተቋማት ድረስ የተለያዩ የኪነሕንፃ፣ የምህንድስና እና የዲዛይን ፕሮጀክቶችን ነድፏል፣ ተግብሯልም። በበርካታ የዲዛይን ውድድሮች በአሸናፊነት ተሸልሟል፤ በአገር ውስጥ እና በዓለማቀፍ ውድድሮች ላይ በዳኝነት አገልግሏል፤ እንዲሁም በምርምር እና በማስተማር መስክ ከግል እና ከመንግሥት ተቋማት በትብብር ሠርቷል። በተጨማሪም፣ ማኀደር የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማኅበር እና የኢትዮጵያ የቅርስ ባላደራ ማኅበር አባል ነው።

ከ1999/2000 ዓ.ም. ጀምሮ፣ ማኀደር በአርኪቴክቸር፣ በምህንድስና፣ በግንባታ እና በከተማ ህይወት ላይ ያተኮረውን "ከቤት እስከ ከተማ" የተባለውን ሳምንታዊ የሬዲዮ ፕሮግራም (ዘወትር ማክሰኞ ማታ ከ2 እስከ 3 ሰዓት፣ በሸገር ኤፍኤም 102.1) በማዘጋጀት ላይ ይገኛል። ፕሮግራሙ በግንባታ ኢንዱስትሪው እና ከዚያም ባሻገር ባሉ ዘርፎች ጠቃሚ የእውቀት እና የመረጃ ምንጭ ነው።

ማኀደር ሐገረሰባዊ ዕውቀትን ከዓለማቀፍ ልምድ እና ዕውቀት ጋር አቀናጅቶ መጠቀም ይበጃል የምል ማኅበራዊ ባለሙያ ነኝ ሲል ራሱን ይገልፃል። በቅርቡ ከከተማ እና ከግንባታ ጋር ተዛማጅ ለሆኑ ዘርፎች የመረጃ እና የዕውቀት እምብርት የሚሆን "ከተማ ማዕከል" ለመክፈት እቅድ አለው።

**የቡድኑ አባላት፦**

ናኦድ ተፈሪ (አርክቴክት - የየማ አርኪቴክቸር ፒኤልሲ ረዳት) እና የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የኪነሕንፃ ተማሪዎች

# VIRTUAL HOPES IN URBAN HOUSING

| Urban Design |
|---|
| 5 May (SAT): Megenagna |
| 6 May (SUN): National Theater |
| 7 May (MON): Bole Medhanialem |
| 9 May (WED): Meskel Square |

**THE PROGRAMME**

The Suk features housing and urban related subjects from the reference of "HOPE" by using digital tools. This experiment is to test how digital possibilities will play their roles in giving hope.

The Suk offers three urban activities:

**This is your home – Experience It**

Virtual Housing of 40/60 schemes with interactive virtual reality gear.

Housing is one of the basic needs of human beings and one of the major urban challenges in Addis Abeba. Different attempts and schemes have been made by the government and private companies. Almost all housing projects are delayed and finished with lower quantiles.

One of the most popular and highly anticipated housing projects in Addis Abeba is the 40/60 schemes, which are delayed with added costs to buyers. Among the many thousands of people registered, some fully paid, a few thousand were able to win the lottery of the almost finished homes.

To this end, we will use our "Ye ketema suk" to show people how it feels to live in apartments and we will select two schemes from the 40/60 typologies and prepare the virtual reality experience of the housing units. Suggestions from participants will be submitted to the relevant government body and the designers of the schemes for consideration in developing future schemes.

Digital travels to selected places – interactive virtual reality tours to places you need to see

Travelling to other countries is quite an expensive and difficult venture for ordinary citizens of Addis Abeba. To give a glimpse, we will virtually take people to some of the most acclaimed and popular spaces and buildings in the world to experience other cities' urban life and architecture.

The reaction of visitors who are willing to be recorded during their virtual reality experience will be documented and screened at the final exhibition at the Goethe-Institut.

**Compare Yourself – Digital Displays of last year's experience**

The result of the analysis from the "It's your city - Build it" and "How tall are you?" experiments from last year will be displayed. Average height of the participants as well as the major responses to surveys will be displayed to encourage participants to compare themselves with the results.



Architect Maheder Gebremedhin (Photo: Behailu Shiferaw)

**THE CURATOR**

Maheder Gebremedhin Borga is the principal architect and manager of the consulting and construction company "Yema architecture plc" established in September 2008 specialized in Architecture, Interior design and construction. He graduated from Addis Ababa University in Architecture and Urban Planning in 1999 and has since then designed and implemented various projects of architecture, engineering and interior design, ranging from private multi-family housings to hospitals and industrial building to recreational and educational facilities. He has been awarded in many design competitions, served as a jury member for local and international competitions and collaborates with private and public institutions in research and teaching. Maheder is also a member of the Association of Ethiopian architects, the Ethiopian Heritage Trust.

Since 2007, he has hosted the weekly radio show "Kebet Eske Ketema", which focusses on architecture, engineering, construction and urban life (Tuesday evening from 8 to 9 pm on sheger fm 102.1). The show is considered an important source of knowledge and information in the construction industry and beyond.

Maheder considers himself a social professional who believes in integrating local knowledge with international exposures. He will soon open the "Urban Center" planned to be the information and knowledge hub for urban and construction related fields in Addis Abeba.

**TEAM MEMBERS**

Naod Teferi (Architect – Yema Architecture PLC apprentice) and architecture students from different Universities

# ፎቶ ቀጭ ቀጭ

| ፎቶግራፊ |
|---|
| 27 ሚያዝያ (ቅዳሜ): መስቀል አደባባይ |
| 28 ሚያዝያ (እሑድ): ቦሌ መድኃኔአለም |
| 30 ሚያዝያ (ማክሰኞ): መገናኛ |
| 2 ግንቦት (ሐሙስ): ቦሌ መድኃኔአለም |



Taking free portraits at last year's Foto Quech Quech (Photo: Julia Sattler)

**ፕሮግራሙ**

ከተማችን አዲስ አበባ እና የከተማዋ የፎቶግራፍ ጥበብ በፍጥነት እየተለወጡ ነው። ብዙዎቹ ነዋሪዎች ግን ካሜራዎቻቸውን አንግተው ከተማው ውስጥ የሚዘዋወሩ ባለሙያዎችን ማየት ምቾት አይሰጣቸውም።

"ፎቶ ቀጭ ቀጭ" ለጎብኚዎቹ የየራሳቸውን ምስል እያነሳ በነፃ ፎቶግራፋቸውን ይሰጣቸዋል። ፎቶግራፎቹ የሚነሱት በተቀነባበረ አውደ ምስል (ባክግራውንድ) ፊት ሲሆን፣ እያንዳንዱ ምስል በትናንት፣ በዛሬ እና በነገ መነፅር፣ የተመረጠው ቦታ ላይ በተካሔዱት ሥፍራዊ ለውጦች፣ ግንባታዎች እና መፈራረሶች እና በሰብዓዊ ለውጦቹ አማካይነት ምላሽ የሚሰጥ ነው።

ፕሮጀክቱ እንደ መስቀል አደባባይ፣ ቦሌ፣ ብሔራዊ ቴአትር እና መገናኛ ባሉ የተለያዩ ቦታዎች ይከናወናል።

ፎቶግራፎቹ እዚያው ወዲያው ታትመው ለተነሺዎቹ በነፃ ይሰጣሉ።

